# ለጸጋዬ

## መታሰቢያነቱ ለፀጋዬ ገ/መድህን (ደብተራው)

ከሂኖክ የሺጥላ

የጥቁር አፈር ሠንበሌጥ፣
ሲመዘመዝ ሲወሰወስ፣
ይወለዳል ጌጥና ፈርጥ::

ጥቁር አፈር እርሱን ዘርታ፣
ዘር አድርታ...
ዘር አፍርታ........
የተዘራው ደሞ ደርቶ.....
ባረንጉዋዴው መቀነቱዋ፣
በለምለሙዋ ላይ አሽቶ.....
ዕውነትን ከሆዱዋ ሰፈር፣
ከሽንት ውኃዋ ተጋርቶ፣
አንድነቱዋን ከታሪኩዋ፣
ውበትዋን ከምነቱዋ ከቶ...
ነብሱን ለክብሩዋ እንደ’ ስለት፣
ጀርባውን ለሳት ሠንሰለት፣
ዕጅ ዕግሩን ደሞ ለብረት...
ግንባሩን ላርማጮሆ ንዳድ...
ለመትማ የቀተር እሳት...
ስንቱ አለፈ....
ግን እያለፈ ገዘፈ.....

የትናንት የአበው ተስፋ፣
የግዜን ገደብ አለፈ...
ህያው...ይኸው...
በኔ በትናንቱ ሽል ነብስ ዘርቶ ተነደፈ......

የሰማዕታት ሕያው ድምፅ፣
ቃል ሆኖ በውስጤ ቢሰርፅ፣
ሚስጥረ ትግሉ በርትቶ፣
ህያውነቱ ጎልብቶ...
ጎልብቶ ቀልቤን ቢገዛው፣
ይሂ የህዝብ ትግል....
ይሂ የአበው የ’ደም ስር፣
ብዕሬን ስንኝ አዘራው::
አንጉዋዬ በትዝታ ምጥ...
በምናብ አለም ዝምታ፣
ፀጥ ባለ ተስፋ ሲናጥ፣
በማይታይ ትግል ሲዋጥ....
ምድሪቱ ወንድ ተነፍጋ...

አድባሩ ዘራፍን ሲያጥጥ....
ቀን ያሳሰበው ዐድር ባይ...
ሆዱ የሸጠው አታላይ፣
በርጩሜው ላይ ሲፈናጠጥ...
ያኔ ነው ባንተ ትዝታ....
ስንኜ ቃል የሚፈታ....::
ያኔ ነው የኔ ዝምታ
ጩኸት ሆኖ፣
ግጥም ሆኖ፣
ስንኝ ሆኖ የሚፈታ::

ሰውና ሰው፣
ያገሬ ሰው፣
አሙዋሙዋትህን ስሰማ፣
ሽል ሳለሁ ተንፈራገጥኩኝ፣
ነብስ አውቄ የልህ ምራቅ፣
የቁጭት ብሶቴን ዋጥኩኝ::

ሰውና ሰው ያገሬ ሰው፣
በአድዋና በማይጨው፣
መሀል አገዳ ሲለያይ፣
በሳንጃና ትክል ድንጋይ፣
ከምንሽሩ ሲወያይ...
(ሰውና ሰው ያገሬ ሰው)
ያን ምህተቡ በጥርስ፣
ወንድ ነበረ አንድ እር'ሱ::
ታድያ !
መድህን ብቻ አይደለም፣
ጎንደሬው በቻ አይደለም፣
ጎጃሜው ብቻ አይደለም፣
ወለጋው ብቻ አይደለም፣
አፋሩ ብቻ አይደለም፣
ጉራጌው ብቻ አይደለም፣
ኢትዮጵያም ፀጋ ተገፎዋት፣
በዘበነኛው ዕፁብ ስልት፣
ቀን በሚሸረው ብልሀት!.....

እባክዎትን አንቱ ጌቶች፣
ይንገሩኝ ስለዚህ ፍጥረት፣
በማር ልውሱ አንደበት፣
ማር ሲልሱ፣
ማር ሲያቀልጡ፣
ማር ሲበሉ ባደጉበት.....
ምን ቢያምን ያንገቱን ፈተው፣ እጁ ላይ ያጠለቁለት፣
በክርም አይደል በብረት!
ሠውተውትም ከሆነ፣
ክቡር ነው እንዲ'ህ ያለው ሞት፣

የቴዎድሮስ የደም ትሩፋት፣
ዕምቢኝ ማለት ለነፃነት፣
ከሲጋ የተቀበረ፣
ያያያዘን ነው ዕ'ንዳጥንት... ::

ታዲያ አሁን ከታሪካቸው፣
ከማሌሊቱ ፉካሬ፣
ምን ሠርቶ ነው የሱ ነገር፣
በምን ልቆ የሱ ወሬ፣
የሆነው ያ'ሳር ገበሬ....?

ኢትዮጵያዊነት አይደለም፣
በአጉል ተስፋ መደንበር፣
ተገነጣጥሎ መያያዝ፣
ዕምነቱንም ማደናገር፣
ጥንትም ቢሆን የሳት ራት ያው የሳት ነች፣
ስሙዋም የሳት ነው ስትበር፣
ብሎ በሽንጎ መንገር፣
የብሶታቸው ባህል ነው፣
በንዲህ ያለው ጎቅ ማበር፣
ስዩመ እግዚአብሔር ለመሆን፣
ከዘመን ዘመን ለመኖር...
አይ ህሊና: ድንቅ ምናብ፣
ቀመናንም አለማፈር...::

ትናንት ከሆዱዋ ወጥቶ፣
ራሱዋ ላይ አመድ ማቡነን፣
መመፃደቅ መተናተን፣
እግር ተከተሎ መጥቶ፣
ጌታችሁ ነኝ ስገዱልኝ፣
በልባችሁ መንበር ሹሙኝ፣
በምነታችሁ ላይ ሰይሙኝ፣
ሳትወለድ እደግ በሉኝ፣
እነ'ዕንትናም ዕዩኝ ዕዩኝ፣
ደሞ እኮ አድባራችሁ ነኝ፣
የናት ያባቴ ከራማ፣
በሕዝቦቹ ላይ የሾመኝ፣
ነግሶ ለመሆን ደጅ አስጠኝ.....
እኔስ እል ነበር የሸጠኝ፣
የራሴን ገፍቼ ከሰው...
የሰውን ሲያስቀላውጠኝ.....
እንዴት ዕላለሁ የሾመኝ፣
በዘረኝነት በሽታ...
ልቤን በንቀት ሲገልበኝ፣
የተገገርነት ልቦና፣
እንደ ዠማ ፈረሰኛ፣
ወንበር ላይ ሲያገላብጠኝ....

መቀመጪያዬ ካናቴ....
ከማሰቢያዬ ሲበለጠኝ.....
እንዴት እላልሁ የሾመኝ....
እኔስ እል ነበር የሸጠኝ....
ብሎ በሸንጎ መንገር፣
የዲሞክራሲው ባህል ነው፣
በንዲህ ያለው ኅቅ ማበር...
ወደ ግዞት ለመወርወር.....
ስዩም እግዚአብሔር ለመሆን...
ከዘመን ዘመን ለመኖር....::

የውኃ ላይ ኩበት ቢያምፅ፣
ዕበት ሆኖ ትል ይወልዳል፣
የናንተን መብከት ለመግለፅ፣
በያመቱ በየካቲት፣
ትግራይ ከበሮ ይመታል...
ግማሽ ሀገሬው በችጋር፣
በምግብ ዕጦት ይሞታል....
ብሎ በሸንጎ መንገር፣
የብሶታቸው ባህል ነው፣
በንዲህ ያለው ኃቅ ማበር፣
ወደ ግዞት ለመወርወር፣
ስዩመ ዕግዚአብሔር ለመሆን፣
ከዘመን ዘመን ለመኖር...::

ለመግዛት ግዛት ለማስፋት፣
በዘር ጠርቶ፣
ከወርቅ መኃለቅ ወጥቶ፣
ምንድን ነው በድንበር መስፋት...
ህዝቡን ጠልቶ፣
ከመሬቱ ጋ!...መጋባት.....
መሬት መግፋት!

በስጋ ሳይዛመዱ፣
በኃሳብ ሳይላመዱ፣
ከልብ ሳይዋደዱ፣
ምንድን ነው ከንቱ መደንፋት፣
በሰው መሬት ከብት መንዳት፣
የማይገፋውን መግፋት፣
ሰው አጥር ላይ...
እግር ማንሳት....
ምንድን ነው ከንቱ መደንፋት፣
ወርቅ ከሆኑ ወርቅ ነው፣
የምን አፈርን ፍለጋ፣
መኖር ነው በወርቅ ሙዳይ፣
ባሸዋ በድንጋይ ዋጋ!

ለራያው ነው ለጎንደሬው፣
የሚጠፋው ያፈሩ መልክ፣
ላርማጮሆው ነው ለሳንጃው ሰው፣
ግር የሚለው የወርቅ እከክ....
ላፋሩ ነው ለዘቦው ሰው የሚጠፋው...የከብቱ ልክ?...

ወርቅ ከሆኑ ወርቅ ነው፣
ምንድን ነው እንደ ዕባብ መሳብ፣
ለወሰንና ለድንበር፣
ቁራጭ ማንነት መነተት፣
የማይመስል ጎረግ መሳብ....::
ወርቅማ ጥንትም ወርቅ ነን፣
የነጠርን አሽንክታብ፣
የትንታግ መኃለቅ ትብታብ...
ገፍላ የገፍላ ድባብ...::

ወርቅ ከሆኑ ወርቅ ነው፣
ግማሽ መደብ: ግማሽ ነሃስ...
ዕርጉም ተፈጥሮን ለማረስ፣
...በመሬቱም ላይ ለማረስ::

ብሎ በሸንጎ መንገር፣
የዲሞክራሲው ባህል ነው፣
በንዲህ ያለው ኃቅ ማበር፣
ወደ ግዞት ለመወርወር፣
ስዩመ ዕግዚአብሔር ለመሆን፣
ከዘመን ዘመን ለመኖር፣
.....
ግና ያ!...ሰውና ሰው፣
ሊያውም የሃገሬ ሠው፣
ያን ማተ'ቡ በጥርሱ፣
ወንድ ነበረ አንድ እሱ::....